# የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 አፈፃፀም መመሪያ ማሻሻያ

## ቁ.02 /2009 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

ነሐሴ 24/ 2009

1.መግቢያ

መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ፣ፍትሀዊነት እና የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት ለማሳደግ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ስርአት ከ1996 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ከነበሩበት ዓመት ጀምሮ ትምህርታቸውን ተከታትለው ተመርቀው የወጡ፣በመከታተል ላይ ያሉና ሲከታተሉ ቆይተው በማንኛውም ሁኔታ ያቋረጡ ተጠቃሚዎች ላይ ሁሉ ለመተግበር የሚያስችል ስርአት ተቀርጾ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/1995 እንዲሁም በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 154/2000 የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2004 የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ከምረቃ በኋላ ግዴታቸውን በገቡት ውል መሰረት በሙያ አገልግሎት በመስጠት ወይም በጥሬ ገንዘብ ክፍያ በመክፈል ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው በተደነገገው መሰረት እየተሰራበት ይገኛል። አሰራሩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፡-

- የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ክፍያን ገንዘብ በመክፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት ግዴታቸውን ለሚወጡ የአገልግሎት አሰጣጥም ሆነ የክፍያ አሰባሰብ ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የመረጃ አሰባሰብና አያያዝ እንዲሁም የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2004 ላይ በህግ ትርጓሜና በአፈፃፀሙ ዙሪያ በየጊዜው ከተጠቃሚዎችም ሆነ ከሌሎች አስፈፃሚ አካላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 አንቀጽ 10/5/ የወጪ መጋራት ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት የሚፈጸምበትን ዝርዝር መመሪያ እንዲያወጣ ለትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት አዳዲስ የስራ መስኮችን ማካተት በማስፈለጉ፣

ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000 አንቀጽ 10/3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቀደም ሲል ወጥቶ ሥራ ላይ የነበረውን የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 001/2004 በማሻሻል ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 02/2009 /2009 ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ ፣

ሀ. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁ.650/2001 ነው፣

ለ. "ደንብ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000 ነው ፤

ሐ. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸዉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነዉ፤

መ. "ተቋም" ማለት በመንግስት አካል ሥር የሚተዳደር ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርት የሚሰጥበትና በማንኛዉም ክልል በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ከፌደራል መንግስት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው፤

ሠ. "አሠሪ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመራቂን ቀጥሮ የሚያሰራ ማንኛዉም የመንግስት መሥሪያ ቤት፣የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም ዓለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሙያዉ በግሉ ሥራ የተሰማራ ሰዉን ይጨምራል፤

ረ. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነው፤

ሰ. "ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም በመንግስት ተቋም ለመማርና የሚፈለግበትን ወጪ ለመክፈል ከተቋሙ ጋር ዉለታ ገብቶ የከፍተኛ ትምህርት ወይም ሥልጠና የሚከታተል ተማሪ ነው ፤

ቀ."ወጪ መጋራት" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚና መንግስት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበት ሥርዓት ነው ፤

በ. "ከምረቃ በኃላ ከገቢ ተከፋይ" ማለት ማንኛውም ተጠቃሚ በገባዉ ውለታ መሠረት የሚጋራውን የወጪ መጠን ከወርሃዊ ገቢው በታክስ መልክ እየቀነሰ የሚከፍልበት ሥርዓት ነው፤

ተ. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል ።

ቸ. "በመምህርነት የሰለጠነ" ማለት፡- ቀድሞ ለመምህርነት ሙያ ተብሎ ለተደራጀ ተቋም የሰለጠነ ወይም በኢንዱስትሪ ፍላጎት ተፈላጊውን የትምህርት መስክ የያዘና የስነ- ማስተማር ወይም ፔዳጎጂ ስልጠና የወሰደ ነው።

4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፤

ከ1996 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ከነበሩበት ዓመት ጀምሮ ትምህርታቸውን ተከታትለው ተመርቀው የወጡ፣በመከታተል ላይ ያሉና ሲከታተሉ ቆይተው፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6.7 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ያቋረጡ ተጠቃሚ ላይ ሁሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

5. የወጪ ድርሻ

5.1.መንግሥት ለምግብና ለመኝታ የሚያወጣውን ወጪ ሙሉ በሙሉና ለትምህርት ከሚወጣው ወጪ ለመነሻ 15% ያላነሰ ተሰልቶ ተጠቀሚዎች ይጋራሉ።

5.2. ተጠቃሚው ሊጋራቸው የማይገቡ ወጪዎች፤

5.2.1. በትምህርት፣በምርምር ወይም በሰባቲካል እረፍት ያሉ መምህራንን ለመተካት የሚቀጠሩ የትርፍ ጊዜ መምህራን ደመወዝ፤

5.2.2. የህክምና ባለሙያዎች የፕሪ-ክሊኒካልና የክሊኒካል አበል

5.2.3. ለመስተንግዶ፣ለፐላንት፣ለማሽነሪ እና ለመሳሪያ ግገር፣እድሳትና ጥገና፣ለሀገር ውስጥ ለስልጠና፣ ለተሽከርካሪ፣ ለሌሎች እንደተሽከርካሪ ላሉ መጓጓዣዎች መግዣ፣ ለሕንፃ፣ ለቁሳቁስ እና ለተገጣጣሚዎች መግገር ሌሎች ክፍያዎች እንዲሁም በቀጥታ በተቋሙ ገቢ በማስገኘት ዓላማ ላይ የተሰማሩ ክፍሎች ሠራተኞች ደመወዝ ይህ መመሪያ እስከሚሻሻልበት ጊዜ ተጠቃሚው እንዲጋራቸው አይጠበቅም፡፡

5.3. የወጪ መደቦች ታሳቢ እና ስሌት፣

5.3.1. የምግብ ወጪ፣

ሀ. በወቅቱ በሚኖረው የመንግስት ተመን መሰረት በዚህ ወጪ መደብ ለእያንዳንዱ ተማሪ የወጣ ወጪ በተጠቃሚው እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

ለ. ከምግብ አቅርቦት ጋር የተያያዘ የሠራተኛ ደመወዝ፣ የመብራት፣ የውሃና የጽዳት ወዘተ... ወጪዎች በሌሎች አስተዳዳራዊ የወጪ መደቦች የሚያዙ ይሆናሉ፡፡

5.3.2. የመኝታ ወጪ፣

ሀ.የመኝታ ወጪ አንድ ተጠቃሚ በተቋሙ የመኝታ አገልግሎት ከተሰጠው በወቅቱ በሚኖረው የመንግስት ተመን መሰረት እንዲከፍል ይጠበቅበታል፡፡ይህም ከመኝታ ክፍልና ከአልጋ በተጨማሪ የመኝታ ክፍሉን የውሃ፣ የመብራትና የጽዳት አገልግሎት ወጪ የሚያካትት ይሆናል፡፡

ለ. በምግብና በመኝታ አገልግሎት ምትክ በጥሬ ገንዘብ የተሰጠው ተማሪም ይኸው በተመሳሳይ የወጣበትን ወጪ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

5.3.3. ከትምህርትና ሥልጠና ጋር ቀጥታ የተገናኙ ወጪዎች፣

ሀ. በሥራ ላይ ያሉ መምህራን ከሚከፈላቸው ደመወዝ ሀያ በመቶ (20%)

ለ. በትምህርት በምርምርና በሳባቲካል/ለተቋሙ ጠቀሜታ ያለው ፕሮጀክት አቅርቦና አጸድቆ በተቋሙ ኃላፊ ለተፈቀደለት/እረፍት ምክንያት ደመወዝ ለሚከፈላቸው መምህራን ከሚከፈላቸው ደመወዝ አስራ አምስት በመቶ (15%)፣

ሐ. የቴክኒካል ረዳቶችና ላቦራቶሪ ሠራተኞች ደመወዝ ሀያ በመቶ (20%)

መ. የውጭ ሀገር መምህራን ደመወዝ በያዙት የአካዳሚክ ደረጃ /Rank/ በተመሳሳይ ኢትዮጵያውያን በሚያገኙት ደመወዝ ተሰልቶ ሀያ በመቶ (20%) ተጠቃሚው እንዲጋራ ይደረጋል።

5.3.4. አስተዳደራዊ ወጪዎች

ሀ. የአስተዳደር ሰራተኞች በዋነኛነት ትምህርትና ስልጠና በአግባቡ እንዲካሄድ የተማሪዎችና የአጠቃላይ ተቋሙ ጥበቃና ድጋፍ የተቀላጠፈ እንዲሆን፣ የተማሪዎች መኝታ ቤቶችና ምግብ ዝግጅት በተገቢው መንገድ እንዲከናወን ወዘተ… አስፈላጊ በመሆናቸው ደመወዝ የሚከፈላቸው በመሆኑ፣ ከእነዚህም ውስጥ ከሰማንያ ፐርሰንት ያላነሱት ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ፣ ለአስተዳደር ሠራተኛ ከሚከፈለው አጠቃላይ ደመወዝ እና ክፍያ የሰማንያ በመቶውን አስራ አምስት በመቶ(15%)፣

ለ. በሥራ ማስኬጃ መደበኛ በጀት ውስጥ በ6257 /ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ/፣6258 /ለቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ክፍያ/ እና 6259 /ለውሃ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ/፣ የተያዙት አገልግሎቶች ወጪ በተወሰነ ደረጃ በተማሪው መኝታ ላይ የተያዙ

በመሆኑ ከጠቅላላ ወጪው ሰማንያ በመቶውን ብቻ በመውሰድ ከዚህ ውስጥ ሃያ በመቶ (20%)፣

ሐ. በሥራ ማስኬጃ መደበኛ በጀት ውስጥ በዚሁ ገጽ በፊደል "ለ" ከተጠቀሱት የወጪ ርዕሶች በስተቀር በሌሎች የስራ ማስኬጃ በጀት ርእሶች ከተያዘው ወጪ አሥራ አምስት በመቶ (15%) ተጠቃሚው እንዲጋራ ይደረጋል፡፡

6. የወጪ መጋራት ውልና አፈፃፀም፣

ማንኛውም በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርት እንዲከታተል የተመደበ ተጠቃሚ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ በየትኛው የክፍያ ዓይነት ወጪ እንደሚጋራ ከተቋሙ ጋር ውል መፈፀም ይኖርበታል፡፡

6.1. ውል የሚፈፀመው፤ በጤናና በትምህርት ሙያ ለሚሰለጥኑና ለሚሰማሩ ተጠቃሚዎች መንግስት በሚመድባቸው ማንኛውም ቦታ በአገልግሎት ግዴታቸውን እንዲወጡ ሲሆን እንዲሁም ለሚ/ር መ/ቤቱ በደንቡ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን በጥናት ላይ ተመስርቶ ወደፊት ከሚያወጣው የሙያ መስክ ዝርዝር ውጪ ባሉ ሙያዎች የሚሰለጥኑ ተጠቃሚዎች ወጪውን በጥሬ ገንዘብ ይጋራሉ፡፡

6.2.. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዲስና ነባር ተማሪዎች ሲመዘገቡ ተጠቃሚው የሚፈለግበትን የግዴታ ዓይነት፣አጠቃላይ ለተጠቃሚው የሚወጣውን ወጪ፣ የሚጋራውን የወጪ መጠን በየሥልጠና መስኩ በመለየትና የማንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በቅድሚያ በመስራት ፎርሙ በትክክል ስለመሞላቱ በማረጋገጥ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በሂደትም ተጠቃሚው ለሚጠይቀው ጥያቄ ማብራሪያ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.3. በሚ/ር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ለየከፍተኛ ትምህርት ተቋሚት በሚላከው የስምምነት ፎርም ላይ ማንኛውም ተጠቃሚ ውል ስምምነት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

6.4. የወጪ መጋራት ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልገሎት የሚፈጸመው በአገልግሎት እንዲወጡ ለተፈቀደላቸው ባለሙያዎች ለሰለጠኑበት ጊዜ እኩል የአገልግሎት ጊዜ በመስጠት ነው፡፡

6.5. እያንዳንዱ ተጠቃሚ እስከ ምረቃ ወይም እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ የሚፈለግበትን የወጪ መጋራት ሂሳብ እና ጠቅላላ ለትምህርቱ የወጣውን ወጪ ተቋማት ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በየትምህርት ዘመኑ ከምረቃ በኋላ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ለሚ/ር መ/ቤቱም በግልባጭ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቋማት ይህንን እና ሌሎች በደንቡ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመወጣት የሚያስችላቸውን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

6.6. አስቀድሞ የከፈለ ተማሪ ትምህርቱን ካቋረጠ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ያለው ወጪ ታስቦ ቀሪው ተመላሽ ይሆንለታል፡፡

6.7. በማንኛዉም የትምህርት ሙያ የሚሰለጥን ባለሙያ ትምህርቱን ሳያጠናቅቅ በማንኛዉም ምክንያት ቢያቋርጥ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተጠቀመውን ወጪ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ትምህርቱን ያቋረጠው በሀገራዊ ጥሪዎችና ተልዕኮዎች ከሆነ ክፍያው መሰረዝ ይኖርበታል፡፡

6.8. በትምህርት ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ማንኛውም የመንግስት ትምህርት ቤት፣ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ የመምህራን ማሰልጠኛ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሌሎች የመንግስት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ተመድቦ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባ ካላገኘም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ በማሳወቅ መረጃ በመያዝ እና በማቅረብ የወጪ መጋራቱን በገንዘብ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

6.9. በጤና ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር/ የክልል ጤና ቢሮ በሚመድበው ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኝ የመንግስት የጤና ተቋማት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ሲኖርበት ምደባ ካላገኘም ከጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር /ከክልል ጤና ቢሮ ማስረጃ መያዝ

ይኖርበታል። በሚያቀርበው መረጃ መነሻነት የወጪ መጋራት ክፍያ ግዴታውን በገንዘብ እንዲወጣ ይደረጋል።

6.10. በአገልግሎት ግዴታዉን ለመወጣት ዉል የፈፀመ ተጠቃሚ እንደተመረቀ ምደባ በወቅቱ አለማግኘቱን ከሚመለከተዉ አካል ማለትም ትምህርትን በሚመለከት እንደአግባብነቱ ከክልል ትም/ቢሮ ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠዉን መረጃ ማቅረብ የማይችል የትምህርት ባለሙያ እና ጤናን በሚመለከት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር /ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር/ ከክልል ጤና ቢሮ መረጃ ማቅረብ የማይችል የጤና ባለሙያ በመንግስት ተቋም በራሱ ተቀጥሮ ቢሰራ ግዴታዉን በአገልግሎት እንደተወጣ አይቆጠርም። ግዴታዉን በገንዘብ ከነመቀጫዉ እንዲወጣ ይደረጋል። ሆኖም ምደባ አለማግኘቱን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል የትምህርት ባለሙያ በመንግስት ትምህርት ቤቶችና ተቋማት በመምህርነት ሙያ እንዲሁም ጤናን በሚመለከት በመንግስት ጤና ተቋማት ተቀጥሮ የሰራ የጤና ባለሙያ ግዴታውን በአገልግሎት እንደተወጣ ይቆጠራል።

6.11. ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በደንቡ አንቀጽ 10/5 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የወጪ መጋራቱን ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት እንዲወጣ የሚፈለግ ማንኛውም ተጠቃሚ ግዴታውን በአገልግሎት መወጣት ይኖርበታል። መንግስት በመደበው ቦታ አገልግሎት መስጠት ያልቻለ ተጠቃሚ በውሉ ላይ የተገለጸውን/የትምህርት15%+የምግብ+የመኝታ/ ድምር ወጪ እና የዚህኑ ወጪ 50% ቅጣት ጨምሮ ይከፍላል። ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት ሰጥቶ ያቋረጠ ተጠቃሚ ያገለገለበት ዘመን ታስቦ ቀሪውን ክፍያ ከነቅጣቱ ገቢ አስገቢው አካል በሚያወጣው የአከፋፈል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል። ተጠቃሚው ቀደም ሲል በሌላ መስክ ተሰማርቶ በገንዘብ መክፈል የጀመረ ከሆነ ቀሪውን ክፍያ ብቻ መንግስት በሚመድበው ቦታ በአገልግሎት እንዲወጣ ይደረጋል።

6.12.. በማንኛዉም የትምህርት መስክ ተመርቀዉ በመንግስት ትምህርት ቤቶች፣በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በመምህራን ማሰልጠኛ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣በሌሎች የመንግስት የማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት በመምህርነት ሙያ ወይም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣በፌደራል፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣በክልል እና ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ሠራዊት አባል የሆኑ ብቻ በምደባም ይሁን በቅጥር በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራቱ በአገልግሎት ሊያዝላቸዉ ይችላል። ሆኖም ግን በከፊል አገልግሎት ሰጥተው ካቋረጡ ቀሪውን የወጪ መጋራት ግዴታቸውን ከነመቀጫዉ ገንዘብ በመክፈል እንዲወጡ ይደረጋል።

6.13. በሀገር መከላከያ ሰራዊት ፣በፌደራል፣በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፣በክልል እና ማረሚያ ቤቶች በፖሊስ ሠራዊት አባልነት ብቻ አገልግሎት የሰጡ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ከሰጡበት ተቋም በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከዕዳ ነጻ ስለመሆናቸው ከባለስልጣኑ ማስረጃ በማቅረብ የትምህርት ማስረጃቸውን ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ማግኘት ይችላሉ።

6.14. በማንኛውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በምደባም ይሁን በቅጥር በመምህርነት ወይም በጤና ሙያ ዘርፍ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.8 እና 6.12 በተጠቀሱት የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በመስራት ላይ እያሉ መንግስት ለስራ ፈልጓቸው በሹመት በመውሰድ በተለያየ የስራ አስፈፃሚነት ደረጃ መድቦ ያሰራቸው ከሆነ በሹመት የተመደቡ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ በማቅረብ ሹመት ከማግኘታቸው በፊት የሰሩበት ጊዜ በአገልግሎት ታስቦ ቀሪውን ግዴታ ያለቅጣት በገንዘብ እንዲወጡ ይደረጋል።

7. ወጪን በገንዘብ የመክፈል ግዴታ ተጠቃሚው ክፍያውን ለመፈጸም ስለሚችልበት ሁኔታ ያሉ አማራጮች፣

ሀ. ትምህርቱን ጨርሶ ወይም አቋርጦ ከቆየ ከአንድ ዓመት የእፎይታ ጊዜ በኋላ በግብር መልክ ከደመወዙ ወይም ከገቢው ላይ ቢያንስ ከመቶ አስር /10%/ ተቀናሽ እየተደረገ ሊከፍል ይችላል፡፡

ለ. ተጠቃሚው ትምህርት በሚከታተልበት በእያንዳንዱ ዓመት የሚፈለግበትን ክፍያ በቅድሚያ ወይም፤

ሐ.ተጠቃሚው እንደተመረቀ ወይም ትምህርቱን እንዳቋረጠ በእፎይታ ጊዜው ውስጥ ክፍያውን በሙሉ በአንድ ጊዜ የሚከፍልበት ሥርዓት ሲሆን በደንቡ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በግብር መልክ ከገቢያቸው ላይ ተቀናሽ እየተደረገ ስለሚከፈል የወጪ መጋራት ክፍያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚያወጣው ዝርዝር የአሰራር ስርአት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ሆኖም በየትምህርት ተቋማቱ ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ ቅድሚያ ክፍያ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ቢያንስ በተሰበሰበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

መ. በደንቡ አንቀጽ 5/1/ መሠረት ትምህርቱ ለሚፈፀመው ጊዜ የሚፈለግበትን ጠቅላላ የወጪ መጋራት በቅድሚያ ለሚከፍል ተጠቃሚ አስር በመቶ /10%/ በየሰሚስተሩ ወይም በየዓመቱ ቅድሚያ ለሚከፍል አምስት በመቶ /5%/ እና ከምረቃ በኋላ በእፎይታ ጊዜ እስከ አንድ ዓመት ለሚከፍል ሦስት በመቶ /3%/ ተቀናሽ እንደሚደረግ በደንቡ የተሰጠው ማበረታቻ ተፈፃሚነቱ እንደተጠበቀ ነው፡፡

## 8. የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ እና ስለቀጣይ ስልጠና ሥርዓት

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት በደንቡ አንቀጽ 12/7 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት ድንጋጌ በአገልግሎት እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት ግዴታ እስኪወጡ ወይም በገንዘብ ግዴታ የገቡ ተጠቃሚዎች ክፍያ እስኪያጠናቅቁ ወይም ለክፍያው የባንክ ዋስትና እስኪያቀርቡ ጊዜያዊም ሆነ ዋናውን የትምህርት ማስረጃና ትራንስክርፕት /ኦፊሻልን ጨምሮ/ የትምህርት መረጃ እንደማይሰጥ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ደንብ አንቀጽ 17 ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ልዩ መመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የመንግስትም ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሙያው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበትን ተመራቂ አገልግሎት መስጠቱ እንዲሁም

በገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ክፍያውን ሳያጠናቅቅ ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀጠል እንደማይኖርበት በተደነገገው መሠረት፡-

ሀ. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህርነት አገልግሎት በመስጠት የሚገኝ ተጠቃሚ ተቋሙ ለድህረ ምረቃ ትምህርት እንዲገባ መፍቀዱ ሲረጋገጥ በተቋሙ ጥያቄ ለድህረ ምረቃ አሰልጣኝ የትምህርት ተቋም፣

ለ. በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የመንግስት መ/ቤቶች እና ተቋማት ተመልሰው ለማገልገል ውለታ በመፈፀም ወደ ድህረ ምረቃ ትምህርት በመስሪያ ቤታቸው ስፓንሰርነት የሚገቡ ተጠቃሚዎች ከተላኩበት መስሪያ ቤት ወይም ተቋም በሚያቀርቡት መረጃ መሰረት ኦፊሻል ትራንስክሪፕትም ሆነ ሌሎች ተጨማሪ የትምህርት መረጃ ለአሰልጣኝ የትምህርት ተቋማት መላክ ይቻላል ፡፡

ሐ. ከላይ ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭ ማንኛውም ግዴታውን ያልተወጣ ተጠቃሚ የድህረ ምረቃ ትምህርት ዕድል ሊሰጠውም ሆነ ሊከታተል አይችልም፡፡

መ. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በገንዘብ ወይም በአገልግሎት ለመክፈል ስምምነት የፈፀመ ወይም የህግ ግዴታውን ያልተወጣ ተመራቂ ወይም ያቋረጠ ተጠቃሚ የገባውንም ሆነ ህግ የጣለበትን ግዴታ እስኪወጣ ድረስ ዋናው የትምህርት መረጃ በተማረበት የትምህርት ተቋም ይቀመጣል፡፡ ሆኖም ለሥራ ስምሪትም ሆነ ሌሎች ሁኔታዎች የሚያገለግል የተጠቃሚውን ስም የትምህርት አይነትና ደረጃ የሚገልፅ "ለሚመለከተው ሁሉ" የሚል ጊዜያዊ ማስረጃ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ ፈፅሞ የተገኝ የትምህርት ተቋም አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሠ. ግዴታውን በክፍያ ለመወጣት ውል የፈጸመ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ወይም ግዴታውን በአገልግሎት እንዲወጣ የሚጠበቅ ሆኖ ውል በማፍረሱ የወጪ መጋራት ግዴታውን በገንዘብ ከነመቀጫው እንዲከፍል የሚገደድ ተጠቃሚ የሚፈለግበትን ግዴታ በውለታው መሰረት መፈጸሙን ወይም ባለመፈጸሙ የሚፈለግበትን ክፍያና ቅጣት ሲያጠናቅቅ ወይም ላለበት ግዴታ ዋስትና ማቅረቡ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሲረጋገጥና ከእዳ ነጻ ስለመሆኑ ከባለስልጣኑ ማስረጃ ሲያቀርብ የሰለጠነበት ተቋም አረጋግጦ የትምህርት ማስረጃውን ይሰጣል፡፡

ረ. በቅድመ ምረቃ በወጪ መጋራት በታሳቢ ተምሮ ያለበትን ግዴታ ሳይወጣ ለድህረ ምረቃ እድል የሚያገኝ ተጠቃሚ በቅድመ ምረቃ የገባው ውል ከድህረ ምረቃ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሰ. ለድህረ ምረቃ ትምህርት ከሚልካቸው የፌደራልም ሆነ የክልል መ/ቤት ወይም ተቋም ከምረቃ በኋላ አገልግሎት ለመስጠት ውለታ ፈፅሞ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በፈፀመው ውለታ መሰረት ለማገልገል ፈቀደኛ ያልሆነ ተጠቃሚ በቅድመ ምረቃ በወጪ መጋራት ከሚጠበቅበት ግዴታ በተጨማሪ ለድህረ ምረቃ ትምህርት የወጣውን አጠቃላይ ወጪ በትምህርት ወቅት ከተከፈለው ደመወዝ ጋር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

ሸ. በድህረ ምረቃ የሰለጠነ ተጠቃሚ ከስፖንሰሩ ጋር የገባውን ግዴታ መፈጸሙ እስኪረጋገጥ ድረስ የትምህርት ማስረጃው በአሰልጣኙ ተቋም ውስጥ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ የሰለጠነበትን ትምህርት ደረጃ የሚገልጽ ማስረጃ "ለሚመከተው ሁሉ" በሚል ሊሰጠው ይችላል፡፡ ለጤና ሙያ ዘርፍ ምሩቃን ግን ዝርዝራቸው ከየማሰልጠኛ ተቋሙ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአስቸኳይ መላክ ይኖርበታል፡፡

ቀ. ማንኛውም የትምህርት ተቋም ከዚህ በላይ ከተገለፀው በደንቡ በተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት ወሰን ውጪ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ያለባቸውን እዳም ሆነ ግዴታ መክፈሉ ሳይረጋገጥ ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ሰጥቶ ከተገኘ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

በ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.8 እና 6.12 በተጠቀሱት ተቋማት በመምህርነት ሙያ ወይም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት በአገልግሎት ግዴታቸውን የተወጡ ባለሙያዎች አገልግሎት ከሰጡበት ከክልል ትምህርት ቢሮ፣ ከቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ፣ ከፌደራል አስፈፃሚ አካላት እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ጤናን በሚመለከት በመንግስት ጤና ተቋማት በአገልግሎት ግዴታቸውን የተወጡ የጤና ባለሙያዎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር/ ከክልል ጤና ቢሮ በሚያቀርቡት የአገልግሎት ማረጋገጫ መሠረት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከዕዳ ነጻ ስለመሆናቸው

ከባለስልጣኑ ማስረጃ በማቅረብ ከሰለጠኑበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የትምህርት ማስረጃቸውን ማግኘት ይችላሉ።

9. ትምህርት ሚኒስቴር፣የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጋራ የሚያከናውኗቸው ተግባራት፣

9.1. የወጪ መጋራት ሥራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሠራተኞች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ በቂ ግንዛቤ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

9.2. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በገንዘብ ክፍያ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ የህግ ክፍተቶችንና የአሰራር ችግሮችን በየጊዜው በመገምገም ሆነ በማጥናት የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፣

9.3. ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ የወጪ መጋራት ስራን ማካተት አፈፃፀሙን መከታተል፣

9.4. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የሚከታተል የሥራ ክፍል ከበቂ የሰው ኃይል ጋር መደራጀቱን መከታተል፣

9.5. ባለድርሻ አስፈፃሚ መ/ቤቶች በደንቡ በተሰጣቸው የስልጣን ሃላፊነት ወሰን መሠረት ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ

9.6. በሚ/ር መ/ቤቱ እንዲሁም ስለገቢው አሰባሰብ ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚወጡ የአፈፃፀም መመሪዎች ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ሥራ መስራት፣

9.7. ባለድርሻ አስፈፃሚ አካላት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የወጪ መጋራቱን ሂደት በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣

9.8. በአፈፃፀሙ ዙሪያ ስላጋጠሙ ችግሮች ቢያንስ በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ በ/ሚር መ/ቤቱ እና በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን

አስተባባሪነት የመወያያ መድረክ በመፍጠር ባሉ አፈፃፀሞች ዙሪያ ውይይት ማካሄድ፣

9.9.ትምህርት የጨረሱም ሆነ ያቋረጡ ተጠቃሚዎች ዋስ ጠርተው የትምህርት ማስረጃ ሊወስድ ስለሚችሉበት ሁኔታ ለሥራው ቅልጥፍና፣ለቁጥጥርና ለክትትል አመቺ የሆነ የጋራ የሆነ ሥርዓት መዘርጋት፣

9.10. በጤናና በትምህርት ሙያ፣ በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት እና የሀገር መከላከያ ሰራዊት፣የፌደራል፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፣የክልል እና ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ሠራዊት አባላት ውጭ ያለ ማንኛውም ተጠቃሚ ሚ/ር መ/ቤቱ በደንቡ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ሥልጣን በአገልግሎት ሊፈፀም ስለሚገባው የሙያ መስክ መመሪያ እስካላወጣ ድረስ ማንኛውም ተጠቃሚ የወጪ መጋራቱን በገንዘብ እንዲወጣ የማድረግ ኃላፊነትና ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

10. የተሻሩ መመሪያዎች ፣

ከወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብም ሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው "የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 001/2004 ተሻሽሎ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

11. የመመሪያው ተፈፃሚነት፤

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 24 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጥላዬ ጌቴ (ዶ/ር)
የትምህርት ሚኒስትር